**በሽግግር ፍትህ ሂደት ዙሪያ ከትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር ልኡካን ቡድን ጋር የተደረገ ውይይት አጭር መግለጫ**

**የፍትህ ሚኒስቴር - አዲስ አበባ**

## 1. መግቢያ

የሽግግር ፍትህ ህዝባዊ ምክክር፥ ግብአት ማሰባሰብ እና ረቂቅ ፖሊሲ የማዘጋጀት መርሀ-ግብሮች በአገር-አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ መደረግ ከጀመሩበት ከህዳር 2015 ዓ.ም ጀምሮ - ሂደቶቹ በትግራይ ክልል ጭምር ያለ እንከን መከናወን የሚችሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት በርካታ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። የፍትህ ሚኒስቴር ከፍተኛ አመራር እና የሽግግር ፍትህ ከፍተኛ ባለሙያዎች ቡድን አባላት ከጊዜያዊ አስተዳደሩ ከፍተኛ አመራር ጋር በመቀሌ የመጀመሪያ ዙር ውይይት አካሂደዋል።[1] በክልል ደረጃ የሚካሄዱ ምክክሮችን አስመልክቶ - ሁለቱም አካላት - በየወቅቱ የተነሱ ስጋቶች ከስር ከስር የሚታዩበት እና የሚቃለሉበትን ሁኔታ ሲያመቻቹ ቆይተዋል። ይህን ተከትሎም - መጀመሪያ በክልሉ ከሚገኙ የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባላት ጋር፥[2] ቀጥሎም በክልሉ አምስት ከተሞች (በሽሬ፣ አክሱም/አድዋ፣ መቀሌ፥ አዲግራት እና ማይጨው) እና በአዋሳኝ ወረዳዎች ከሚገኙ የተለያዩ የክልሉ ማህበረብ አባላት ጋር የተሳኩ የምክክር እና ግብአት ማሰባሰብ መርሃ-ግብሮች ተካሂደዋል።[3]

ቀጥሎም - የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን በክልል ደረጃ የሚካሄዱ ዋና ዋና ምክክሮች መጠናቀቃቸውን ተከትሎ - የክልል እና የፌዴራል መንግስቱ አመራሮች የሚገኙበት የሁለት ቀናት ከፍተኛ የምክክር መድረክ በቢሾፍቱ ከተማ አካሂዷል።[4] የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር አመራር በመርሀ-ግብሩ ላይ እንዲገኝ ሐምሌ 26 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ጥሪ ቢደረግለትም - ጳጉሜ 2015 ዓ.ም በሰጠው ምላሽ 'አስቀድመው በተያዙ ተደራራቢ የስራ ፕሮግራሞች ምክንያት በመድረኩ ላይ መገኘት' የማይችል መሆኑን አሳውቋል።

ይሁን እንጂ አስተዳደሩ በመድረኩ ላይ ባይሳተፍም ከሽግግር ፍትህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የሚያነሳቸው በርካታ ጉዳዮች ያሉ በመሆኑ - በነዚህ ነጥቦች ዙሪያ 'ከፌዴራል መንግስቱ ከፍተኛ አመራር ጋር ጥልቀት ያለውና ግልጽ መፍትሄዎችን ማስቀመጥ የሚያስችል የሁለትዮች ውይይት' የሚካሄድበት ሁኔታ እንዲመቻች ጥያቄ አቅርቧል። በጥያቄው መሰረት - ስብሰባው በፍትህ ሚኒስቴር መስከረም 25 2016 ዓ.ም ተካሂዷል።

## 2. በውይይቱ ከትግራይ ልኡክ ቡድን የተነሱ ዋና ዋና ነጥቦች

በእለቱ በሌ/ጀነራል ፃድቃን ገብረትንሳኤ የተመራው የልኡካን ቡድን በሽግግር ፍትህ ስራው አገራዊ ጥቅም እና አስፈላጊነት ላይ ልዩነት ባይኖርም - ከሂደቱ እና አደረጃጀቱ ጋር በተያያዘ ያለውን ስጋት፥ ቅሬታ እና ሀሳብ በዝርዝር አቅርቧል። ዋና ዋና ነጥቦቹም የሚከተሉት ናቸው።

ሀ) የሽግግር ፍትህ ሂደቱ በፕሪቶሪያ ስምምነት ላይ በተቀመጠው መሰረት እየተመራ አይደለም፥ በዚህም ምክንያት ከሂደቱ አሰራር፥ አቀራረጽ ወይም አደረጃጀት የሚመነጩ አሉታዊ ተጽእኖዎች ተንፀባርቀዋል። በቀጣይም - ቀደም ሲል የተጀመሩ ስራዎች ቢኖሩ እንኳ - የሽግግር ፍትህ ስራው ዋና መሰረት ይኸው ስምምነት መሆን አለበት። ስምምነቱ የሁለትዮሽ እንደመሆኑ መጠን የፍትህ አጀንዳው ትግራይን ማእከል በማድረግ - ሌሎች ጉዳዮችን ሳያደባልቅ - መካሄድ ይኖርበታል፥ ከዚህ ውጭ ከተኬደ ግን ውጤት የሚገኝበት አይሆንም።

ለ) የፕሪቶሪያው ስምምነት ከሽግግር ፍትህ ውጭ በርካታ ጉዳዮችን የያዘ ነው። ስለሆነም አፈፃፀማችን ሁሉን-አቀፍ መሆን ይኖርበታል። የሽግግር ፍትህ ስራው - ከተፈናቃዮች፥ የረድኤት አቅርቦት፥ ዲሞቢላይዜሽን እና ሌሎች አንኳር ጉዳዮች ጋር በተቀናጀ መንገድ ባለመካሄዱ በዚህ ማእቀፍ ማምጣት በምናስበው ዘላቂ ሰላም ላይ የራሱ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል። አልፎም አሰራሩ - በጊዜያዊ አስተዳደሩ ውስጥ የውጥረት፥ የመነጠል እና የክፍፍል ምክንያት ሆኗል።

---

[1] April 2023
[2] 29 July 2023 Mekelle
[3] 31 July – 5 August 2023
[4] 8-9 September 2023 Bishoftu

ሐ) የሽግግር ፍትህ ሂደቱ የትግራይን ልዩ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ የተመራ አይደለም። የትግራይን ሁኔታ የተለየ የሚያደርጉ በርካታ ተጨባጭ ሁነቶች አሉ። ካለፈው ጥሰት/ጥፋት ጋር የሚያያዘው የስብራት ስሜት ግዙፍ ነው፣ በምእራብ ትግራይ እና ድንበሮች አካባቢ የቀጠሉ ጥሰቶች አሉ፣ የኤርትራ ሀይሎች ጥፋት ሊሸፈን ይችላል ወይ የሚለው ጥያቄ አሳሳቢ ነው፣ የተፈናቃዮች እና አስተዳደር ወሰን ጉዳዮች ምላሽ አላገኙም፣ በፌዴራል መንግስቱ ችላ የተባሉ የኢኮኖሚ/ማህበራዊ ጉዳይ ጥያቄዎችም አሉ።

በድምር ሲታይ ተጨባጭ ወቅታዊ ሁኔታው የሽግግር ፍትህ ስርአት ለመዘርጋት መጣደፍን የሚጠይቅ አይደለም። አሁን በተጀመረው መንገድ ዘላቂ ፍትህ እና ሰላም ማረጋገጥ የሚቻል አይሆንም። ወቅቱ - ሁሉም ጉዳይ በጥሞና ታይቶ - በተመጋገበ መንገድ መሄድ ያለበት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። የሽግግር ፍትህ ሂደቱን ከማፋጠን ይልቅ በእርጋታ እንዲመራ ከራሳችን፣ ከክልሉ ምሁራን እና በምክክሮቹ ላይ ከተሳተፈው ማህበረሰብ ጥያቄ ቢቀርብም ተቀባይነት አላገኘም።

መ) የሽግግር ፍትህ የአቀራረጽ ሂደት እና አደረጃጀት የትግራይን ወሳኝ ተሳትፎ ባካተተ መልኩ የተመራ አይደለም። ስራውን የሚመራው የፌዴራል መንግስት ሲሆን - ትግራይ በማእከላዊ መንግስት የትኛውም የስልጣን እርከን ምንም ውክልና የላትም። በመሆኑም ጥቅሟን በተሟላ መንገድ ማስጠበቅ የምትችልበት እድል የለም። የሽግግር ፍትህ ሂደቱን አሁን ባለው መንገድ ማስኬድ በውጤታማነቱ እና ህዝባዊ ቅቡልነቱ ላይ አንፃራዊ ተጽእኖ ያሳድራል። ከምክክር ባለፈ - ህዝቡን እና ክልሉን - ከጥናቱ መሰረት እስከ ፖሊሲ ማጽደቅ እና ትግበራ ማሳተፍ ያስፈልጋል።

ሠ) የሽግግር ፍትህ ስራ በክልሉ ለደረሰው ከባድ ጥሰት/በደል እውቅና ከመስጠት ይጀምራል። ይህ ተደርጓል ወይ?

ረ) የፍትህ ጥያቄ ከፍ ያለ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ አለው። የተጓደለ ስልጣን ያለው የክልል አስተዳደር ይዞ - በሽግግር ፍትህ ማእቀፍ በስታራቴጂያዊ ጉዳይ ላይ መወሰን ይቻላል ወይ? ይህ ሁነት በአስተዳደሩ ላይ ከባድ የፖለቲካ ቅቡልነት ጫና እንዲያደርር ምክንያት በመሆኑ በደንብ ሊጤን ይገባዋል።

ሰ) የፌዴራል መንግስት ራሱ ተከሳሽ ሆኖ ሲያበቃ - የሽግግር ፍትህ ስራ ሂደት መሪ ሆኖ መምጣቱ ከመሰረታዊ የፍትህ መርህ ጋር የሚፃረር ነው። ይህን ለማስቀረት ምን እናድርግ በሚለው ላይ ብንወያይ?

ሸ) የሽግግር ፍትህ አማራጭ ሀሳቦች ሂደው ሂደው ለአገር-አቀፍ የምርመራ እና ዳኝነት ስርአት ሙሉ ስልጣን የሚሰጡ መሆናቸው አይቀርም። አለማቀፋዊ ስርአት ተፈፃሚ የሚሆንበት እድል የለም። ይህም የኤርትራ ሀይሎችን ጥፋት በአግባቡ እንዳይታይ ያደርገዋል።

3. **ለልኡካን ቡድኑ አባላት የተሰጡ ማብራሪያዎች**

በእለቱ ለልኡካን ቡድኑ ሰፊ ማብራሪያ ተሰጥቷል።

ከሽግግር ፍትህ ማእቀፍ ውጭ ሌሎች ተቋማትን አስመልክቶ የተነሱ ነጥቦች በሌላ መድረክ የሚታዩ ይሆናል።

ሀ) የሽግግር ፍትህ መሰረት የፕሪቶሪያ ስምምነት ነው የሚለውን በተመለከተ፦ ቀደም ሲልም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል የተጀመረ ጥናት የነበረ ሲሆን፣ እ.ኤ.አ በህዳር ወር 2021 ላይ በወጣው የጥምር ቡድኑ የምርመራ ውጤት ላይም የሽግግር ፍትህ ተግባራዊ እንዲደረግ ምክረ-ሀሳብ መቅረቡ እና መንግስትም ይህን በመርህ ደረጃ መቀበሉ ግልጽ ነው። ያም ሆነ ይህ በየትኛውም ሁነት መነሻነት የሚመጣ የሽግግር ፍትህ ስራ ምሉእ የሆነ ወይም አማራጮችን የዘጋ ስላልሆነ - በተጨማሪ ይዘት ላይ ያተኮረ ሀሳብ ቢቀርብ የተሻለ ነው።

ለ) በጥቅሉ የፕሪቶሪያው ስምምነት ከሽግግር ፍትህ ውጭ ካሉ በርካታ ጉዳዮች ጋር የተያያዘ መሆኑ፣ ትግበራ ለመጀመር አሁን ጊዜው አለመሆኑ ወይም ምቹ ሁነት አለመኖሩን በተመለከተ፦ አሁን እየተካሄደ ያለው የምክክር እና የፖሊሲ ማርቀቅ ሂደት ብቻ ነው። የሌሎቹ ተዛማጅ ጉዳዮች መኖር ወይም የሁነቶች ምቹ አለመሆን በራሳቸው የምክክር እና የፖሊሲ ማርቀቅ ስራዎችን የሚከለክሉ አይሆኑም። የቀረበው ሀሳብ - በዋናነት በፖሊሲው ማስፈፀም ምእራፍ የሚነሳ ስጋት ነው።

ሐ) የሽግግር ፍትህ ሂደቱ የትግራይን ልዩ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ የተመራ አይደለም የሚለውን በተመለከተ፦ በፕሪቶሪያው ስምምነት መግባባት ላይ የተደረሰው ሀገር-አቀፍ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማእቀፍ ለማዘጋጀት ነው። የሚዘጋጀው ማእቀፍ ክልሎችን የሚመለከት የርእስ ትኩረት (thematic focus) ሊኖር ይችላል፣ አሊያም ልዩ ከባቢያዊ ሁኔታዎች የሚስናገዱበትን እድል ሊፈጥር ይችላል። ነገር ግን በትግራይ ላይ አተኩሮ ይደራጅ የሚለው ሀሳብ ከስምምነቱ መንፈስ የራቀ፣

ችግርም የሚያስነሳ አካሄድ ነው። ሲቀጥልም - ትግራይ ውስጥ ያለውን ውስብስብ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ከከፍተኛ የፖለቲካ አመራሩ ጋር፡ እንዲሁም በክልሉ ካለው የአካዳሚክ ማህበረሰብ ጋር በመቀሌ ሁለት ዙር ዝርዝር ውይይት መካሄዱ - ሂደቱ ለክልሉ ልዩ ሁኔታ እውቅና የሰጠ መሆኑን የሚያመላክት ነው።

መ) የሽግግር ፍትህ የአቀራረጽ ሂደት እና የአባላቱ አደረጃጀት የትግራይን ወሳኝ ተሳትፎ አላየም የሚለውን በተመለከተ፦ ካሁን ቀደም የተሰጡ የተሳትፎ እድሎችን አስተዳደሩ እና የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ያልተጠቀሙባቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ - አሁንም ተሳትፎን ለማረጋገጥ የተጀመረውን ሂደት አጠናክሮ መሄድ ወሳኝ/አስፈላጊ መሆኑን ማስረገጥ ያስፈልጋል።

ሠ) የሽግግር ፍትህ ስራው በክልሉ ለደረሰው ከባድ ጥሰት/በደል እውቅና ይሰጣል ወይ የሚለውን በተመለከተ፦ በቅድሚያ የጥምር ቡድኑ የምርመራ ውጤት ብዙ የጥሰት ግኝቶችን ማውጣቱ እና መንግስትም ብዙዎቹን ሀላፊነቶች መቀበሉ ማስታወስ ያስፈልጋል። በተጨማሪም መንግስት ራሱ ያካሄዳቸው ምርመራዎች (ለምሳሌ በአክሱም) የጥፋት ግኝት መመስረታቸው፡ ይህም በወቅቱ ይፋ መደረጉ ይታወቃል። እንዲያም ሆኖ - እስካሁንም ያልታዩ በርካታ ጥፋቶች ያሉ በመሆኑ ነው የሽግግር ፍትህ ማእቀፍን መዘርጋት የግድ የሆነው።

ረ) የክልሉ አስተዳደር የተጓደለ ስልጣን ይዞ እንደ ፍትህ ባለ ስትራቴጂያዊ ጉዳይ ላይ መወሰን ይቻላል ወይ የሚለውን በተመለከተ፦ የሽግግር ፍትህ ሂደትን የሚመሩ ከበቂ በላይ አስገዳጅ የአለም-አቀፍ መርሆች እና አሰራሮች ያሉ እንደመሆኑ መጠን የክልሉ አስተዳደርም ሆነ የኢትዮጵያ መንግስት የሚጨምሩት/የሚፈጥሩት ትልቅ አዲስ ነገር አለ ማለት ያዳግታል። በይዘት ደረጃ ፖሊሲው ከነዚህ መርሆች ተፃራሪ ሊሆን አይችልም። ሲቀጥልም ጉዳዩ የህዝብ እንጂ የፖለቲካ መዋቅሩ ወይም ልሂቁ ውሳኔ ሊሆን አይገባም።

ሰ) የፌዴራል መንግስት ተከሳሽ የሚሆንበት እድል እያለ የሽግግር ፍትህ መሪ ሆኖ መምጣቱ ከፍትህ መርህ ጋር የሚፃረር ነው የተባለውን በተመለከተ፦ መንግስት ጉዳዩን በዚህ መልክ መምራቱ - በመንግስት መዋቅር ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው በግለሰብ ደረጃ ተጠያቂ ሊሆን አይችልም የሚለውን አረዳድ የሚያጭር አይደለም። ይልቁንስ ሙግቱ መሆን ያለበት መንግስት ቁመናውን ተጠቅሞ ከአለማቀፍ ደረጃ በታች የሆነ ፖሊሲ እንዳያወጣ እንዴት ጥረት ማድረግ ይቻላል የሚለው መሆን ነበረበት። ከዚህ ውጭ ግን ማንኛውም ፖሊሲ የሚወጣበት አሰራር መንግስትን ማእከል በማድረግ የሚፈፀም መሆኑ የተለመደ አሰራር ነው።

ሸ) በሽግግር ፍትህ ሂደት አለማቀፍ የህግ/ተጠያቂነት ስርአት ተፈፃሚ የሚሆንበት እድል አለመኖሩን በማስመልከት የቀረበው ሀሳብ፦ ነገሮችን ከስረ-መሰረት ለማየት ያህል - ባለፉት አመታት መንግስት በተለይ በICHREE ስልጣን ማእቀፍ የተቋሙን ማንዴት በሁነት ላይ ተመስርቶ ለመቀበል በርካታ ገንቢ አማራጮችን አቅርቦ እንደነበር ማወቅ ያስፈልጋል። ሆኖም ተቋሙ በወቅቱ ፍጹም ፖለቲካዊ አቋም እና ምልከታን ለማራመድ በመምረጡ መንግስት ትብብር ከማድረግ ለመቆጠብ ተገዷል። መሰረታዊ ነጥቡ - አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ወቅት መንግስት ቁርጠኝነቱን በዚህ ልክም ግልፆ የነበረ መሆኑ ነው።

### 4. ስምምነት የተደረሰበት ሀሳብ እና ቀጣይ ስራ

ከተሰጡት ማብራሪያዎች እና የመግባቢያ ነጥቦች በመነሳት - ክልሉ በውስጡ ያለውን ከፍተኛ አቅም በማደራጀት በፖሊሲ አማራጭ ሰነዱ ላይ የተመለከቱ ሀሳቦችን የሚተች ይሁን አማራጭ ሀሳቦችን በቴክኒካል ደረጃ ዝርዝሮ የሚያቀርብ ስራ ለመስራት እና በተሻለ የባለቤትነት ስሜት በሂደቱ ላይ እንዲሳተፍ ስምምነት ላይ ተደርሷል። ዝርዝር ምልከታውንም ለባለሙያዎች ቡድኑ የሚያጋራ ይሆናል። ዝርዝር አፈፃፀሙም በየጊዜው እየተገናኙ የሚወሰን ይሆናል።

ከዚህ ባለፈም በባለሙያዎች እይታ አልፈው አሁንም እልባት የማያገኙ ጉዳዮች ካጋጠሙ እንደአስፈላጊነቱ በፖለቲካ አመራር ሊታዩ እንደሚችሉ መግባባት ላይ ተደርሷል።